# የምሁራን ደናቁርት ፪

‘የምሁራን ደናቁርት’ በሚል ኣርእስት ቀደም ብለን ያወጣነው ጽሑፍ ለጥቂት ሰዎች የዓይን መክፈቻ ሆኗቸዋል። ጥቂቶቹንም ከተሳሳተ ኣቋም እንዲመለሱና እንዲጸጸቱም ያደረጋቸው ኣሉ። በዚሁም ኣርእስት ቀጥለን፣ የነዚህን የጥቂት “ምሁራን ነን” ባዮች ተግባር ፍጹም የዕብድ ሥራ እንጂ የጤና ሰው ኣለመሆኑን ለማሳየት እንሞክራለን።

በመጀመሪያ ምሁራኑ ከማን ጋር ነው የሚፈረጁት ብሎ መጠየቁ ደግ ነው። ከዚህ በፊት የእርዳታ ሆነ የብድር ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይላክ፣ ወይም እንዳይገባ የከለከሉና ያስከለከሉት እነማን ናቸው ብለን ብንጠይቅ መልሱን በቶሎ እናገኘዋለን። መልሱን ስናገኝም ምሁራኑ ፍርጃቸው ከእነማን ጋር መሆኑ በግልጽ ለማየት ይቻላል።

በተቀዳሚ የምትጠቀስ ለረዥም ጊዜ የጉሮሮ ዕንቅርት የሆነችብን ጐረቤታችን ግብፅ ስትሆን፣ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ለዓባይ ወንዝ ግድብ መሥሪያ ከዓለም ባንክ ብድር በጠየቀች ጊዜ የኣሜሪካን መንግሥት ለምና ብድሩ እንዳይሰጠን ያስከለከለችን[1] ናት። ቀጥሎም በቅርቡ በዕንቅርታችን ላይ ጆሮ ደግፍ የሆነብን የትላንቱ ወንድማችን፣ የዛሬ ምቀኛችን፣ የኤርትራው ኢሳያስ ኣፈወርቂ፣ በድርቁ ዘመን ለእርዳታ የተላከልን እኽል በሱዳን በኩል መጥቶ በኤርትራ እንዳያልፍና[2] እንዳይገባልን የከለከለ ሰው ነው። ይህም ለመቸም ጊዜ የማይረሳ በደልና ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪካዊ ጠባሳ ትቷል።

የእነዚህን የሁለት ዓመጸኞች ነገር ሲያሳዝነን የሚኖር ሁኔታ እያለ ታድያ፣ ዛሬ ብሎ-ብሎ የገዛ ወገኖቻችን፣ ወንድሞቻችን የሆኑት ኣጉል ምሁራን ከገዢው ፓርቲ ጋር በያዙት እንካስላቲያ ዓይናቸው ታውሮ፣ የሃገርና የሕዝብን ዕድገት ለመግታት እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ለመከልከል ሕግ በማርቀቅ ተሰማርተው ስናይ፣ ‘ኣረ ምን ሆኑ! ምንስ ነካቸው? እንዴትስ ዓይናቸው ታወረ? የሕዝብ ጉዳይና የፖለቲካ ቁርቋስን መለየት እንዴት ተሳናቸው?’ እያልን እንደነቃለን። እጅግም ያሚያሳዝን ነው!

እንግዲያውስ እኒህ የምሁራን ደናቁርትን ከነዚህ ከጣምራ ጠላቶቻችን ጋር ኣብረው፣ ግንባር ገጠም ሆነው፣ በእናት ሃገራቸው ላይ የባዕድ ጫና እንዲጣልባት በመጣራቸው ከሓድያን ብለናቸዋል። የሃገርን ያህል ዓብይ ጉዳይ ስቶ፣ ከጠላት ጋር ግንባር ገጠም ቆሞ፣ በሃገሩ ላይ እርምጃ የሚወስድ፣ ወይም ለማስወሰድ ያሚጥር ሁሉ ለከሓዲነቱ ምንም ጥርጥር የለውም። ስለዚህም ይህን የሚያደርግ ሁሉ በክሕደት ወንጀል ሊከሰስ፣ ተገቢ የሆነና ሕጉ የሚፈቅደውን ሙሉ እርምጃም እንዲወሰድበት ይገባል እንላለን።

ማንኛውም የሃገራችን ውስጣዊ የፖለቲካ እንካስላትያ፣ ኢትዮጵያ ነፃ ሃገር እስከሆነች ድረስ በልጆችዋ ብቻ ይፈታል፤ እናም የሃገር ውስጣዊ የፖለቲካ ጉዳይ በባዕድ እጅና በባዕድ መንግሥታት እንዲፈታ የሚያመለክቱ፣ የሚጥሩና የሚሯሯጡ፣ የባዕድንም እጅ ወደ ሃገር ጉዳይ ጣልቃ ለማስገባት የሚጣጣሩት ከሓዲዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ውስጣዊ የፖለቲካ ውዝግብ በኢትዮጵያውያን እንጂ በማንም ሌላ የባዕድ ግለሰብ ሆነ የባዕድ መንግሥት ኣይፈታም። ይህ ለሁሉም ሰው ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

1. http://nazret.com/blog/index.php?title=nile_restrictions_anger_ethiopia&more=1&c=1&tb=1&pb=1
2.http://topics.nytimes.com/top/reference/timestopics/organizations/u/united_nations/index.html?query=ERITREA%20(ETHIOPIA)&field=geo&match=exact